FEDERAL ETHICS AND ANTI-CORRUPTION COMMISSION

# የመሬት ሀብት አስተዳደር እና የጸረሙስና ትግል በኢትዮጵያ

## (ለግንዛቤ ማስጨበጫ የቀረበ የመወያያ ሰነድ)


**አዘጋጆች**

*ገዛኸኝ ጋሻው*

*ሃረጎት አብርሃ*

*የኋላሸት ደሳለኝ*

*ከፍያለው ዓለሙ*



**ሰኔ 2/2015**

**አዲስ አበባ**

**ማውጫ**


| ተቁ | ርእስ | ገጽ |
|---|---|---|
| 1. | *መግቢያ*___ | |
| 2. | **ክፍል አንድ** *በኢትዮጵያ የመሬት አስተዳደር መርሆዎችና ህግ ማእቀፎች*___ | |
| 3. | **ክፍል ሁለት** *በመሬት ሀብት አስተዳደር ላይ ከሙስና ጋር ተያያዥነት ያላቸው መረጃዎች* | |
| 4. | **ክፍል ሶስት** *በመሬት ሀብት አስተዳደር የግልጽነትና ተጠያቂነት አሰራር ስርአት ፈተናዎች* | |
| 5. | **ክፍል አራት** *በመሬት አስተዳደር ላይ የሚፈጸም ሙስናና ብልሹ አሰራርን በመከላከል ዙሪያ የሌሎች አገሮች ተሞክሮ*___ | |
| 6. | **ክፍል አምስት** *በመሬት አስተዳደር ላይ የሚፈፀም ሙስና ለመከላከል እና ለመወጋት የባለድርሻ አካላት ሚና*___ | |

## I. መግቢያ

መሬት የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ ድህነትን ለማጥፋትና ዘላቂ ልማትን ለማረጋገጥ፣ እንዲሁም የዜጎችን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ቁልፍ መሳሪያ ነው። ከዚህ የተነሳ መሬት ለሰው ልጅ የሕልውና መሠረት ነው ማለት ይቻላል። ይሁንና መሬት የተፈጥሮ ሥጦታ እንደመሆኑ መጠን መጠኑም እንዲሁ በተፈጥሮ የተወሰነ ነው። የሰው ልጅ አምርቶ የሚፈጥረው ሀብት አይደለም።

በመሬት ዘርፍ የሚፈጸመው ሙስና ለከፍተኛ ማህበራዊና ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ምስቅልቅል ምክንያት ነው። ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል የተባለው አለም አቀፍ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት እ.ኤ.አ በኖቬምበር በ2019 "የመሬት ዘርፍ ሙስናን በመዋጋት በአፍሪካ- መልካም ተሞክሮዎች" በሚል ባጠናው ጥናት መሰረት በአለም ላይ ከአምስት ሰው አንድ ሰው የመሬት አገልግሎቶችን ለማግኘት በጎቦ መልክ ክፍያ እንደሚፈፅም ሲያመለክት ከሰሀራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገራት ደግሞ ይህ ችግር በመጨመር የሚያሳይ ሲሆን በዚህም ከሁለት ሰው አንዱ በተመሳሳይ መልኩ የመሬት አገልግሎትን ለማግኘት ጉቦ እንደሚከፍል ጥናቱ ያመለክታል።

በዘርፉ የሚስተዋለውን ሙስና ለመቅረፍ  በርካታ ስራዎች የተሰሩ ቢሆንም አሁንም በመሬት ዘርፍ የሚታየው ሙስናና ብልሹ አሰራር ህዝብን እያማረረና እያስለቀሰ የቅሬታ መነሻ ሆኗል። በዘርፉ ያለው በሽታ እንደ ካንሰር ስር የሰደደ እንደመሆኑ መድሃኒቱን ለመፈለግና ለመዳን ብርቱ ትግል ይጠይቃል። ዜጎች፣ የመንግስት አካላት እንዲሁም ሌሎች ባለድርሻ አካላት በዘርፉ የሚታየውን ሙስና ለመዋጋት ሊመክሩና የበኩላቸውን አስተዋጽ ሊያደርጉ ይገባል።

የፌደራል የሥነምግባርና የፀረሙስና ኮሚሽን በመሬት ዘርፍ ላይ እየተስተዋለ ያለውን ሙስናና ብልሹ አሰራር ለመከላከል የሚመለከታቸው ባድርሻ አካላት ሃላፊነታቸውን እንዲወጡ የምክክር መድረክ አዘጋጅቷል። ይህ ሰነድም ለውይይት መነሻ ይሆን ዘንድ የተዘጋጀ ነው።

## ii.የሰነዱ ዓላማ፡

የዚህ ሰነድ ዓላማ በመሬት ሀብት አስተዳደር ላይ የሚስተዋለውን ሙስናና ብልሹ አሰራር ለመከላከል የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ የሚጠበቅባቸውን ሚናቸውን ባግባቡ እንዲወጡ ግንዛቤ መፍጠር ነው።

# ክፍል አንድ

# በኢትዮጵያ  የመሬት አስተዳደር መርሆዎችና ህግ ማእቀፎች

## 1.1 መርሆዎች

በኢትዮጵያ በመሬት ያለ የንብረት መብት እንዴት መደላደል እንዳለበት፣ መሬትን የመጠቀም፣ የመቆጣጠር፣ የማስተላለፍ መብቶችንና የመሳሰሉትን ጉዳዮች ለመወሰን በተለያዩ ወቅቶች የከተማና ገጠር መሬት አዋጆችን እያወጣች ተግባራዊ ስታደርግ ቆይታለች፡፡ መሬትን ባግባቡና በእንክብካቤ ለመጠቀም፣ በኢፌዲሪ ህገመንግስት አንቀፅ 40 ላይ የሚከተሉት የመሬት አስተዳደር ዋና ዋና መርሆዎች ተመላክተዋል፡፡

- መሬት የሕዝብና  የመንግስት ስለመሆኑ፤
- መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ ስለመሆኑ፤
- መሬት  የጋራ  ንብረት ስለመሆኑ፤
- አርሶ አደር መሬት በነፃ ስለማግኘትና ከመሬት ያለመነቀል መብት፤
- መንግስት መሬቱን ለህዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውና ሲወስደው ተመጣጣኝ ካሳ ስለመክፈል፡፡

## 1.2 የህግ ማእቀፎች

በህገ መንግስቱ የተቀመጡትን የመሬት ፖሊሲዎች  ተግባራዊ ለማድረግ የወጡ ዋና ዋና  የህግ ማእቀፎች፤

- የኢፌዲሪ ህገመንግስት
- የከተማ መሬትን በሊዝ ስለመያዝ የወጣ አዋጅ ቁጥር 721/2004
- የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 456/1997
- ስለከተማ ፕላን የወጣ አዋጅ ቁጥር 574/2002
- የከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 818/2006
- ለህዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበት ፣ ካሳ የሚከፈልበት እና ተነሺዎች መልሰው የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 1161/2011

# ክፍል ሁለት

## በመሬት ሀብት አስተዳደር ላይ ከሙስና ጋር ተያያዥነት ያላቸው መረጃዎች

### 2.1 ሙስናና ብልሹ አሰራርን የሚመለከቱ አገራዊ መረጃዎች

#### 2.1.1 የክልልና ከተማ አስተዳደር መረጃዎች

መሬት ለሙስናና ብልሹ አሰራር ተጋላጭ ከሆኑ ዘርፎች መካከል በቀዳሚነት የሚጠቀስ ነው፡፡ ሙስናና ብልሹ አሰራርን በተመለከተ በአገራችን ባለፉት ሁለት አመታት (በ2014 እና 2015ዓም) የቀረቡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ዘርፉ ለሙስና ተጋላጭ እንደሆነ ጠቋሚዎች ናቸው፡፡ መረጃዎቹ ከአፋር ክልል በስተቀር ከሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የተገኙ ናቸው፡፡

ሰንጠረዥ 1. መሬት ላይ የመጡ ቅሬታዎች/ጥቆማዎች እና በምርመራ ላይ ያሉ የመሬት ጉዳዮች/ኬዞች

| ተ.ቁ | ክልል/ከተማ አስተዳደር | 1.1. የጥቆማ ብዛት | | ድምር | 1.2. በምርራ ላይ ያሉ የመሬት ጉዳዮች/ኬዞች/ | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከተማ | ገጠር | | ከተማ | ገጠር | |
| 1 | አማራ | 7 | 6 | 13 | 2 | 4 | 6 |
| 2 | አዲስ አበባ | 1963 | | 1963 | - | | - |
| 3 | ሲዳማ | 4 | 5 | 9 | 2 | 1 | 3 |
| 4 | ቤ/ጉምዝ | 3 | - | 3 | 1 | - | 1 |
| 5 | ሶማሊ | 194 | 127 | 321 | 113 | 63 | 176 |
| 6 | ደ/ምዕራብ | 38,160.915 ካሬ | 105.5 ሄክታር(105 500) | 143660.915 | 100,022.915 | 37.5 | 100059.5 ካሬ |
| 7 | ሐረሪ | 12 | 2 | 14 | 4 | - | 4 |
| 8 | ጋምቤላ | 24 | 9 | 33 | 4 | 1 | 5 |
| 9 | ደቡብ/ብ/ብ | 17 | 11 | 28 | 3 | - | 3 |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 10 | ኦሮሚያ | - | - | | - | - | - |
| 11 | ድሬዳዋ | 531 | 260 | 791 | 141 | 96 | 237 |
| | ድምር | 2755 | 420 | 3175 | 270 | 165 | 436 |

ከላይ በሰንጠረዥ 1፡ መረዳት እንደሚቻለው ባለፉት ሁለት አመታት በበ2014 እና በ2015 ዓም በክልሎች፣ በአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች በከተማ እና በገጠር ደረጃ መሬት ላይ የመጡ ቅሬታዎችን/ጥቆማዎችን እና በምርመራ ላይ ያሉ የመሬት ጉዳዮች/ኬዞችን ነው፡፡

በዚሁ መሰረት የቀረበ ጥቆማዎችን በተመለከተ አማራ ክልል 13፣ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር 1963፣ በሲዳማ ክልል 9፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል 3፣ ሶማሌ ክልል 321፣ ሀረር ክልል 14፣ በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር 791፣ ጋምቤላ ክልል 33፣ ደቡብ ክልል 28 ጥቆማ የቀረበበት ሲሆን ኦሮሚያ ክልል ቅሬታ ወይም ጥቆማ ያልቀረበበት ክልል መሆኑን ያሳያል፡፡

በምርመራ ላይ ያሉ የመሬት ጉዳዮችን ስንመለከት ደግሞ አማራ ክልል 6፣ ሲዳማ ክልል 3፣ ቤ/ጉሙዝ ክልል 1፣ ሶማሌ ክልል 176፣ ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር 237፣ ሀረሪ ክልል 4፣ጋምቤላ ክልል 5 እና ደቡብ ክልል 3 በምርመራ ላይ ያሉ የመሬት ኬዞችን ያሉባቸው ሲሆን አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና ኦሮሚያ ክልል ደግሞ ምንም አይነት በምርመራ ላይ ያሉ ኬዞች የሌሉባቸው ናቸው፡፡

ሰንጠረዥ 2. በክስ ሂደት ውሳኔ ያገኙ እና በእግድ ላይ የሚገኙ የመሬት ጉዳዮች

| ተ.ቁ | ክልል/ከተማ አሰተዳደር | 2.3.ውሳኔ ያገኙ የመሬት ጉዳዮች/ኬዞች ብዛት | | ድምር | 4.በእግድ ላይ ያለ መሬት በካሬ | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከተማ | ገጠር | | ከተማ | ገጠር | |
| 1 | አማራ | 5 | 2 | 7 | 33,326.22 | - | 33,326.22 |
| 2 | አዲስአበባ | 418 | - | 418 | 9,823 | - | 9,823 |
| 3 | ሲዳማ | 2 | 4 | 6 | 10,000 | - | 10,000 |
| 4 | ቤ/ጉምዝ | - | - | የለም | 102,760 | - | የለም102,760 |
| 5 | ሶማሊ | 33 | 43 | 76 | 120,000 | 244,429 | 364,429 |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 6 | ደ/ምዕራብ | - | - | የለም | - | 33,850 | 33,850 |
| 7 | ሐረሪ | 10 | - | 10 | 3,400 | - | 3,400 |
| 8 | ጋምቤላ | 7 | 3 | 10 | | 138 ሄ/ር(138,000 ካሬ) | 138 ሄ/ር(138,000 ካሬ) |
| 9 | ደቡብ/ብ/ብ | 14 | 11 | 25 | - | - | የለም |
| 10 | ኦሮሚያ | - | - | የለም | 2567,392.9 | - | 2567,392.9 |
| 11 | ድሬዳዋ | 390 | 164 | 554 | - | - | የለም |
| | ድምር | 879 | 227 | 1,106 | 2,846,701.9 | 392,429 | **ጠ/ድ 3,239,130** |

ሰንጠረዥ 2፡ በክልሎች እና በከተማ አስተዳደሮች ውሳኔ ያገኙ የመሬት ጉዳዮች /ኬዞችን እና በእግድ ላይ ያለ መሬትን የሚመለከት ነው፡፡ በገጠርና በከተማ ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮች/ኬዞችን በተመለከተ በአማራ ክልል 7፣ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር 418፣ በሲዳማ ክልል 6፣ በሶማሌ ክልል 76፣ በሐረሪ ክልል 10፣ በጋምቤላ ክልል 10፣ በደቡብ ክልል 25 ሲሆኑ ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር 554 **ሲሆን** ቤ/ጉሙዝ ክልል፣ ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ እና ኦሮሚያ ክልል ደግሞ ምንም አይነት ውሳኔ ያገኙ የመሬት ጉዳዮች/ኬዞች የሉም፡፡

ሌላው በሰንጠረዥ 2 የተመላከተው በእግድ ላይ ያለ መሬት በካሬ ሲሆን ይህም በአማራ ክልል 33,326 ካሬ፣ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር 9,823 ካሬ፣ በሲዳማ ክልል 10,000 ካሬ፣ በሶማሌ ክልል 120,000 ካሬ፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል10 ሄ/ር (10,000 ካሬ)፣ በሀረር ክልል 3,400 ካሬ፣ በጋምቤላ ክልል 138 ሄ/ር (138,000 ካሬ፣ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል 102,760 እና በኦሮሚያ ክልል ደግሞ 2,567,392.9 ካሬ መሬት እግድ ላይ መሆኑን ያመለክታል፡፡ምንም አይነት መሬት በእግድ ላይ የሌለባቸው ደግሞ ደቡብ ብ/ብ/ህ ክልል እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ናቸው፡፡

ሰንጠዥ 3. በህገወጥ መንገድ የተያዘ እና የዳነ መሬት

| ተ.ቁ | ክልል/ከተማ አስተዳደር | 5.በህገወጥ መንገድ የተያዘ መሬት በካሬ | | ድምር | 6.ከህገ ወጥ ይዞታነት የዳነ መሬት በካሬ | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከተማ | ገጠር | | ከተማ | ገጠር | |
| 1 | አማራ | 224,512.25 | - | 224,512.25 | 61,152 | 25,900 | **87,052** |
| 2 | አዲስአበባ | 296,248 | - | **296,248** | 240,081 | - | **240,081** |
| 3 | ሲዳማ | 10,000 | 10,000 | **20,000** | 830.6 | 57,830 | **58,660.6 ካሬ** |
| 4 | ቤ/ጉምዝ | 102,760 | - | **102,760** | 102,760 | - | **102,760** |
| 5 | ሶማሊ | 230,000 | 570,000 | **800,000** | - | - | **አልተገለፀም** |
| 6 | ደ/ምዕራብ | 38,160.915 | 105, 500 | **143,660.915** | 4,288 | 58,000 | **62,288** |
| 7 | ሐረሪ | 28,000 | - | **28,000** | 20,300 | - | **20,300** |
| 8 | ጋምቤላ | - | - | **የለም** | - | - | **የለም** |
| 9 | ደቡብ/ብ/ብ | - | - | **የለም** | 65,000 ካሬ የተያዘ እና -15,800 ካሜ ህገወጥ ኢንቨስተመንት የተሰጠ | 177,660 ካሬ | **258,460 ካሬ** |
| 10 | ኦሮሚያ | 1,450,555 ካሬ(መረጃው በሀለቱም የመጣ) | | **1,450,555 ካሬ** | - | 489,974 ካሬ | **489,974 ካሬ** |
| 11 | ድሬዳዋ | 88,000 | - | | - | 88,000 ካሬ | **88,000 ካሬ** |
| | ድምር | 1,017,681 | 580,105.5 | **3,153,182.165** | 510,211.6, | 839,362 | **ጠ/ድ-1,407,494.6** |

ከላይ በሰንጠረዡ የተመላከተው በክልሎች እና በከተማ አስተዳደሮች በህገ ወጥ መንገድ የተያዘ እና ከህገወጥ ይዞታ የዳነ መሬት ነው፡፡ በህገወጥ መንገድ የተያዘ መሬትን በተመለከተ በአማራ ክልል 224,512.25ካሬ፣ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር 296,248ካሬ፣ በሲዳማ ክልል 20,000 ካሬ፣ ቤኒሻንጉል ክልል 102,760ካሬ፣ ሶማሌ ክልል 800,000, በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል

143,660.915፣ በሀረር  ክልል 28,000ካሬ፣ በኦሮሚያ ክልል ደግሞ 1,450,555 ካሬ ሲሆን ደቡብ ክልል፣ ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር  እና ጋምቤላ ክልል በህገወጥ መንገድ የተያዘ መሬት የሌለባቸው ናቸው፡፡

በሌላ በኩል ከህገወጥ ይዞታነት የዳነ መሬት ስንመለከት በአማራ ክልል **87,052 ካሬ**፣ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር **240,081 ካሬ**፣ በሲዳማ ክልል **58,660.6** ካሬ፣ በቤ/ጉሙዝ ክልል **102,760** ካሬ፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል **62,288**፣ በሀረር  ክልል 20,300 **ካሬ**፣ በደቡብ ክልል **258,460 ካሬ ካሬ** ፣ በኦሮሚያ ክልል **489,974** ካሬ እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ደግሞ **88** ሄክታር (**88,000** ካሬ) መሬት መሆኑን ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል ሶማሌ ክልል እና ጋምቤላ ክልል ላይ ከህገ ወጥ ይዞታነት የዳነ መሬት የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡

ከዚ መረጃው መረዳት እንደሚቻለው በሁለቱ አመታት በአጠቃላይ **1,407,494.6 ካሬ** መሬት ከህገ ወጥ ይዞታነት መዳኑን እንረዳለን፡፡

## ሰንጠረዥ 4 ተጠያቂነትን ማረጋገጥ የሚመለከት መረጃ

በህገ ወጥ የመሬት ማስተላለፍ ተጠያቂ የሆኑ አመራሮችና ባለሙያዎች የሚመለከቱ መረጃዎች ከዚህ በታች በሰንተረዥ የቀረበ ሲሆን ፤ ይህን መረጃ አስመልክቶ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውጭ ከሌሎች ክልሎች ወይም ከተማ አስተዳደር መረጃ አልቀረበም፡፡

| **ተጠያቂ አካላት** | **የተወሰደ እርምጃ** |
|---|---|
| 1. በህገ ወጥ የመሬት ማስተላለፍ ተጠያቂ የሆኑ **አመራሮች** ብዛት | ፖለቲካዊ እርምጃ የተወሰደባቸው 43 የክ/ከ እና 112 የወረዳ አመራሮች ሲሆኑ ዝርዝራቸው ወደ ፍትህ የተላከ 113 የክፍለ ከተማ እና  143 የወረዳ አመራሮች ናቸው |
| 2. በህገ ወጥ የመሬት ማስተላለፍ ተጠያቂ የሆኑ **ፈፃሚዎች** ብዛት | አስተዳደራዊ እርምጃ የተወሰደባቸው 88 የ ክፍለ ከተማ  እና 10 የወረዳ ባለሙያወች ናቸው |

ሰንጠረዥ 4፡ በአዲስ አበባ ከተማ ደረጃ በህገ ወጥ የመሬት ማስተላለፍ ተጠያቂ የሆኑ አመራሮችና ባለሙያዎችን የሚመለከት ሲሆን ፖለቲካዊ እርምጃ የተወሰደባቸው 43 የክ/ከ እና 112 የወረዳ አመራሮች ሲሆኑ ዝርዝራቸው ወደ ፍትህ የተላኩ ደግሞ 113 የክፍለ ከተማ እና 143 የወረዳ

አመራሮች ናቸው፡፡ በባለሙያ ደረጃ ደግሞ 88 የክፍለ ከተማ እና 10 የወረዳ ባለሙያወች አስተዳደራዊ እርምጃ እንደተወሰደባቸው መረጃው ያሳያል፡፡

### 2.1.2 ከፌደራል ፍትህ ሚኒስቴር የቀረበ መረጃ

**ሰንጠረዥ5 ፤በፌዴራል (ከፍትህ ሚ/ር) ከመሬት ጋር ተያይዞ የተፈጸሙ የሙስና ወንጀል ምርመራ፣ ክስና የሀብት ማስመለስ ስራዎች በተመለከተ የተገኘ ሪፖርት**

| ተ.ቁ | ጉዳዩ<br>የመሬትካሳ ክፍያ እና የመንግስት ቤቶች አስተዳደር | የመዝገብ ብዛት | የተጠርጣሪ /ተከሳሽ ብዛት | የተያዘ ተከሳሽ ብዛት | ያልተያዘ | የደረሰ ጥቅም ወይም ጉዳት | የታገደ ሀብት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ምርመራ ላይ ያሉ | 56 | 234 | | | 200,055,690 ብር(ሁለት መቶ ሚሊየን ሃምሳ አምስት ሺህ ስድስት መቶ ዘጠና ብር) 14 የመንግስት ቤቶች | |
| 2 | ክስ የቀረበባቸው | 10 | 303 | 103 | 200 | 27,529 ካ.ሜ 11 ኮንደሚኒየም ቤቶች<br>121,387,881 ብር | |
| | ድምር | 66 | 537 | 103 | 200 | (241,449) ሁለት መቶ አርባ አንድ ሺህ አራት መቶ አርባ ዘጠኝ<br>321,443,571(ሶስት መቶ ሃያ አንድ ሚሊየን አራት መቶ አርባ ሶስት ሺህ አምሰት መቶ ሰባ አንድ)<br>25 የመንግስት ኮንደሚኒየም እና ቤቶች | 11ኮንዶሚንየም<br>81,000ካሬ<br>ይዞታ<br>17,000,000<br>ብር6 ቤት<br>13 ተሽከርካሪ |

ሰንጠረዥ 5 የሚያሳየው በመሬት ካሳ ክፍያ እና የመንግስት ቤቶች አስተዳደር ጉዳይ ሲሆን በፍትህ ሚ/ር የሙስና ወንጀሎች ዳይሬክቶሬት ጀኔራል መረጃ መሰረት ክስ የቀረበባቸው የመዝገብ ብዛት 10፣ የተጠርጣሪ/ተከሳሽ ብዛት 303፣ የተያዙ ተከሳሽ ብዛት 103፣ ያልተያዙ ተከሳሽ ብዛት ደግሞ 200 ሲሆኑ የደረሰ ጥቅም ወይም ጉዳት በሚመለከት ደግሞ 27,529 ካ.ሜ መሬት፣ 11 ኮንደሚኒየም ቤቶች እና 121,387,881 ብር ላይ አሉታዊ ጉዳት ደርሷል፡፡ የታገደ ሃብትን በሚመለከት ደግሞ 11 ኮንዶሚንየም (የጋራ መኖሪያ ቤት) ፣81,000 ካሬ ይዞታ መሬት ፣17,000,000 ብር፣ 6 ቤት እና 13 ተሽከርካሪ መሆናቸውን መረጃው ያሳያል፡፡

# ክፍል ሶስት

# 3. በመሬት ሀብት አስተዳደር የግልጽነትና ተጠያቂነት አሰራር ስርአት ፈተናዎች

## 3.1. የሥነምግባር ችግር

ከመሬት ጋር በተያያዘ ለሚፈጸም ሙስና አብይ ምክንያቱ የሥነምግባር ጉድለት ነው፡፡ በዘርፉ አገልግሎትን የሚሰጡ ስነምግባር የጎደላቸው ባለሞያዎች የተለያዩ አገልግሎቶችን በዘር፣በቋንቋ፣በሃይማኖት፣በፖለቲካ ፓርቲ፣ በጉርብትና በማድላት የሌሎችን ጥቅም ይጎዳሉ፡፡ የእነሱን አገልግሎት ፈልጎ የሚመጣ ተገልጋይን ቀና ምላሽ ከመስጠት ይልቅ ማጉላላት፣ ቸልተኛ ወይም ግዴለሽ መሆን ይስተዋላል፡፡

በተለይ የከተማ ቦታ ዝግጅት፣ ሽንሽና፣ አሰጣጥ እና የቦታ ተመን አከፋፈል አድሏዊ አሰራር ከሚስተዋልባቸው አሰራሮች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

በሌላ በኩልም ነባር ይዞታን ለማረጋገጥ ፣የመሬት መረጃ ለማግኘት፣የመሬቱን የታሰበለትን አጠቃቀም ለመቀየር፣የይዞታ መሬቱን በህገወጥ መንገድ መጠኑን ለማሳደግ፣የስም ንብረት ዝውውር ለማድረግ የማይገባ ጥቅም (ጉቦ) ይጠየቃል፡፡ በተጨማሪም የመሬት አጠቃቀም እቅድን ያልተከተለ ግንባታ ሲገነባ ዝም ብሎ ለማለፍ ጉቦ ይከፈላል፡፡ ከዚህ ባሻገር መረጃን ሆን ብሎ በማጥፋት፣ በመደበቅ፣ በማዛባት፣ በማለዋወጥ፣ ጉቦ መጠየቅ ግልጽነትና የተጠያቂነትን ለማረጋገጥ የሚገጥሙ ፈተናዎች ናቸው፡፡

በተጨማሪም ስነምግባር የጎደላቸው ባለሞያዎች የሃሰት የመሬት ማስረጃዎች ፣ የሃሰት የመሬት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ዝግጅቶችም ስነምግባር በጎደላቸው ባለሞያዎችና

የስራ ሃላፊዎች የሚስተዋል ነው፣ ሀሰተኛ የመኖሪያ ቤቶች ህብረት ሥራ ማህበራትን በማቋቋም የማህበሩ አባለት በህገወጥ መንገድ መሬት እንዲወስዱ ሁኔታዎችም የሚመቻቹበት ጊዜ አለ፡፡ እነዚህ የስነምግባር ችግሮች ግልጽነትና ተጤቂነትን ለማስፈን በሚደረግ ትግል ውስጥ ብርቱ ፈተናዎች ናቸው፡፡

## 3.2. የመሬት ሃብት መረጃዎች ባግባቡ አለመደራጀት

በመሬት ሀብት አስተዳደር ሌላው የግልጽነትና ተጠያቂነት ፈተና መረጃዎች ባግባቡና በጥራት ያለመደራጀት ፈተና ነው፡፡ በከተማ ውስጥ የሚገኙ ቦታዎች የሚሰጡት የአገልግሎት አይነት፣ የያዙት ግለሰቦች ስም፣ በቦታው የሰፈረው ንብረት አይነት ወዘተ…ተለይተው በዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ዘዴ አለመመዝገባቸው፤ የመሬት መረጃ አያያዝ ለቁጥጥር የማይመች መሆኑ፣ የተሰጡ ቦታዎች ይዞት በተደራጀና በተሟላ መንገድ አለመሆኑ፤ የክፍት ቦታዎች መረጃዎች ቁጥጥር አይነት ባግባቡ አለመመዝገብ በመሬት ሃብት አስተዳደር የሚስተዋሉ የመረጃ አያያዝ ክፍተቶች ናቸው፡፡ ከዚህ ባሻገር በየቢሮው ያሉት የመሬት ጉዳይ ፋይሎች አቀማመጥ በዘፈቀደ መሆኑ አሰራሩን ለሙስና ተጋላጭ ያደርገዋል፤ የፋይል ቅብብሎሽ ተገቢው ቁጥጥር የማይደረግበት መሆኑም ተጨማሪ የግልጽነትና የተጠያቂነት ፈተናዎች ናቸው፡፡

## 3.3. የመሬት ህግ እና ደንብ የማውጣትና የማስፈጸም ክፍተት

በመሬት ሃብት አስተዳደር ዙሪያ ከሚከናወኑ ተግባራት መካከል የፖሊሲ፣ አዋጅና ደንቦችን ማውታት የመጀመሪያው ነው፡፡ ፖሊሲዎች አዋጆችና ደንቦች በሚወጡበት ጊዜ አንዳንድ ቡድኖች ድብቅ ፍላጎታቸውን ለማሳካት ሲሉ በአወጣጡ ሂደት ተጽእኖአቸውን ሊያሳርፉ ይችላሉ፡፡

ለምሳሌ ህግን መሰረት ያደረገ ነገር ግን ፍትሃዊ ያልሆነና ምክንያታዊነቱ አሳማኝ ባልሆነ ምክንያት መሬት ምደባ፣ ዋጋ ትመና ስርአት ሊዘረጋ ይችላል፡፡ እንዲህ አይነቱ አሰራር ለሙስናና ብልሹ አሰራር በር የሚከፍት ሲሆን፤ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ፖሊሲዎች፣አዋጆችና ደንቦች ባግባቡ ያልተናበቡ በሚሆኑበት ጊዜ፣ ወይም የሚያሰራ መመሪያና ደንብ በበቂ ሁኔታ አለማዘጋጀት ለሙስናና ብልሹ አሰራር በርከፍታል፡፡የግልጽነትና ተጠያቂነትን አሰራር ለማረጋገጥ ፈተና ይሆናል፡፡

ለህዝብ ጥቅም ነው በሚል ሰበብ አልሚ ነን ለሚሉ ሰዎች በጉቦ መሬት መስጠት፤ የመሬት ዋጋ በሚተመንበት ጊዜ መሬቱ ማውጣት ካለበት ዋጋ በታች ወይም በላይ

መተመን፤ ለመሬት ተነሺዎች የሚሰጥ የማካካሻ ክፍያን ከፍ ወይም ዝቅ በማድረግ ፈቃደ ስልጣንን ያላግባብ መጠቀም ግልጽነትና ተተያቂነትን ፈተና ውስት ይጥላል፡፡ ለባለሀብቶች ቦታ ከመስጠት በፊት ቦታዉ /ከማንኛውም የይገባኛል ጥያቄ ነጻ ሳይሆን፣ ለመንግሥት ወይም ለቀበሌ ቤት ወይም በቦታው ለነበሩ አርሶ አደሮች ተገቢ ካሳ ሳይከፈል ሕግና ደንብ ከሚፈቅደው ውጭ መስጠት፡፡

### 3.4. ደካማ ክትትልና ቁጥጥር

በመሬት ሃብት አስተዳደር ስራዎች ውስጥ ሌላው የግልጽነትና የተጠያቂነት ፈተና የሚመነጨው ከደካማ ክትትልና ቁጥጥር ስርአት ነው፡፡ ለምሳሌ አንዳንድ አልሚዎች የጠየቁትን መሬት ከወሰዱ በኋላ ወደ ልማት እንዲገቡ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር አለማድረግ፤ በሊዝ የተላለፉ ቦታዎች በብዛትና በስፋት ታጥረው የተቀመጡና አንዳንዶቹም የተባለው ግንባታ ሳይገነባ ተከራይተው ለሌላ አገልግሎት የሚውሉበት ሁኔታ ከተገቢ ቁጥጥርና ክትትል ባለማድረግ የሚከሰቱ ናቸው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ አልሚዎች ለአካባቢው ህብረተሰብ የሚገቡት ውለታ ወይም ግዴታዎች በተገቢው መንገድ ክትትልና ቁጥጥር ስለማይደረግበት ውለታው የውሃ ሽታ ሆኖ ይቀራል፤ ለሌቦችም ሙስና ውስጥ የሚገቡበት እድል ይፈጥራል፡፡

### 3.5. የመሬት ወረራ መስፋፋት

በከተሞች አዋሳኝ አካባቢ የሚገኘው የመሬት ሀብት በሕገ ወጥ መንገድ በወረራ መያዝ፣ ከፕላን ውጭ የሆኑ ግንባታዎች እንዲከናወኑ መፍቀድ፤ ሽንሽኖ ያልተደረገባቸውን ቦታዎች ሲወረሩ ዝም ማለት፤ በሕገ ወጥ መንገድ ያአግባብ ለመሬት ግዥ እና ግንባታ መፈፀም ፤

### 3.6. ችግሩን ለመከላከል የዜጎች ተሳትፎ አናሳ መሆን

በመሬት ላይ ያለውን የሙስናና ብልሹ አሰራር ችግር ለመቅረፍ ዜጎች ትልቅ ድርሻ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይሁን እንጅ አንዳንድ ስነምግባር የጎደላቸው ዜጎች ችግሩን አይቶ እንዳላዩ በማለፍ፣ ብሎም በህገወጥ መንገድ ግንባታ ለማከናወን ለደንብና ቁጥጥር ሰራተኞች የማይገባ ገንዘብ መስጠት፣ መሬትን በህገወጥ መንገድ መውረር፣ ሌሎች አገልግሎቶችን ለማግኘት መብትን በገንዘብ መለወጥ ሌላኛው የግልጽነትና ተጠያቂነት ፈተናዎች ናቸው፡፡

# ክፍል አራት

## 4. በመሬት አስተዳደር ላይ የሚፈፀሙ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች በመከላከል የሀገራት ተሞክሮ

አህጉራዊ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ የተከናወኑ ጥናቶች እንደሚያሳዩት መሬት እና የመሬት አስተዳደር ስርዓት ለሙስና በእጅጉ ከሚስቡ ወይም የተጋለጡ ሴክተሮች በከፍተኛ ደረጃ የሚቀመጥ መሆኑን ያሳያሉ፡፡ የዘመነ የመሬት አሰተዳደር ፓሊሲ፤ ግልፅነትና ተጠያቂነት ያለው ሰርዓት አለመዘርጋት ፤ መሬት አሰተዳደር ሚና ያላቸውን አካላት በቅንጅት እና ብትብብር አለመስራት ፤ ከመሬት ጋር በቀጥታ ይሁን በተዘዋዋሪ ግኑኝነት የለውን ማህበረሰብ እና ቤተሰብ በመሬት አስዳደር ዙሪያ ያለውን ተሳትፎ አንሰተኛ መሆኑን ፤ የዘመነ እና በቴክኖሎጂ የተደገፈ የመሬት የመረጃ መረጃ አሰተዳደ ሰርኣት አለመኖር እንዲሁም በዘርፉ ሙስና እና ብልሹ አሰራር የተሳተፉ አካላት ጠንካራ ተጠያቂነት አለመኖሩ በዘርፉ ያለው ሙስና ስር የሰደደ እንዲሆን እና ችግሩን ለመቅረፍ አደጋች የሚያደርጉ ዋነኛ ችግሮች መሆናቸውን በዙሪያው የተካሄዱ ጥናቶች የሚያሳዩ ሲሆን በተለይም ከሳህራ በታች ያሉ አገሮች ችግሩ በእጅጉ ግዝፎ ይታያል፡፡ የእኛ አገር ነበራዊ ሁኔታ ሲታይም በዘርፉ ሙስና ለመከላከል ብዙ ጥረቶች ቢደረጉም ዘርፉ አሁንም ለሙስና በከፈተኛ ደረጃ የተለጠ ዘርፍ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡ በዘርፉ ያለው ደካማ የአሰተዳደር ሰርዓት ላይ ሙስና ተጨምሮ ችግሩ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ አድርጎታል፡፡

በመሬት አሰተዳደር ዙሪያ የሚከሰቱ ሙስና ብልሹ አሰራሮች ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመከላከል እና አሰራሩ ቀለጣፋ ፤ ግለፅ እና በተጠያቂነት ላይ የተመሰረተ የመሬት አስተዳደር ስርዓት እንዲኖር ከማድረግ አኳያ አገሮች የተለያዩ እርምጃዎች ይወሰዳሉ ፡፡ በተለይም በዘርፉ የሚከሰተውን ሙስናና ብልሹ አሰራር ከመከላከል አኳያ የተሻለ ልምድ ያላቸው አገሮች ልምድ መውሰድ ሀገራችን ኢትዮጵያ ለምታደረገውን ሁለ አቀፍ የሙስና መከላከል ስጥረት በእጅጉ ያግዛታል፡፡ ለማሳያ ያክል የሚከተሉት አገሮች በስኬታማነታቸውን ማንሳት ይቻላል፡፡

### 4.1 ዩጋንዳ

የዩጋንዳ መንግስት ከቅኝ ግዛት መውጣት ቡሃላ በሀገርቱ የሚገኘውን የመሬት አሰታደር ስርዓት የተበታተነ ፤ ከተማ እና ገጠር፤ ነጭ እና ጥቁር ላይ የመብት ልዩነት የሚፈጠር የነበረ ሲሆን ከሁሉም በላይ የነበረውን የአስተዳደር ስርዓት በጣም ደካማ እና ለሙስና በእጅጉ የተጋለጠ አሰራር የነበረ ነው፡፡ ይህን አሰተዳደር ለማሻሻል ዩጓንዳ የተለያዩ ተቋማት በማቋቋም ችግሩን ለመፍታት ጥረት ያደረገች ቢሆንም የተሳካ ለውጥ ማምጣት አልቻለችም ፡፡ ነገር ግን ከ2019 ጀምሮ የገጠር እና የከተማ

የመሬት አስተዳደር ግልፅ እና ተጠያቂነት ላይ የተመሰረተ ለማድረግ በቴክኖሎጂ የተደገፈ ሀገራዊ የመሬት አስተዳደር መረጃ ስርዓት (Uganda National Land Information System ( UGLIS ) ተግባራዊ ያደረገች ሲሆን የዚህ ሲስተም ዋና ዓላማም ዜጎች ስለ መሬት አስተዳደር ( ምዝገባ ፤ አቅርቦት ፤ አስተዳደር እና ልማት ) ላይ የተማላ መረጃ እንዲኖራቸው የሚመለከታቸው የመንግስት ተቋማት ፤ ዲፓርትመንቶች ) መረጃ እንዲኖራቸው እና እንድያውቁት ለማድረግ ነው ፡፡ ይህን ሲስተም ከአጠቃላይ ህዝቡ ከ20-27 % በዚህ ሲስተም የመሬት መረጃው የተመዘገበ ሲሆን የዚህ ዋና ዓላማ ትኩረት መሬት ውስን ሀብት በመሆኑ ከብክነት ለመከላከል እና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመከላከል ነው ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሲስተሙ የምዝገባ መረጃ እና አጠቃላይ ለገበያ ( ሪልስቴት ) የሚውልን የግብይት መረጃ ለመስጠት ያግዛል፡፡ በአሁን ሰዓት ተግባራዊ እየተደረገ ያለው በላይኛው የመንግስት መዋቅር ሲሆን በቀጣይ በታችኛው መዋቅር ( Sub-county ) ተግባራዊ ለማደረግ እቅድ እንዳለ ከተገኘው መረጃ ለማወቅ ተችላል፡፡ ይህን ሲስተም በመዘርጋቱ ቀያሶች (Surveyor) ፤ በንኮች ፤ የህግ ባለሙያዎች ፤ ኦዲተሮች ብቻ ሳይሆን ህዝቡ የመሬት ግብይቱ ( Land Transanction ) ተከታትለው ለማወቅ ጠቅሟል፡፡ በአጠቃላይ ሲስተሙ በመዘርጋቱ የሚመለከታቸው አካላት በተለይም ህግ አስከባሪ አካላት በመሬት የሚፈፀሙ ወንጀሎች ለመከላከል ትልቅ አስተዋፀኦ ያደረገ ሲሆን ቀደም ሲል የነበረውን የመሬት ወረራ እና ሽምያ ጋፐ እንዲል እንዳረገው ከተገኘው ጥናት ለማወቅ ተችላል፡፡ ባንኮች ከሲስተሙ ጋር በቀጥታ ለማገናኘት በእቅድ የተያዘ ሲሆን በቀጣይ በፋይናንስ ዘርፍ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ለመከላከል የራሱ አስተዋፀኦ ይኖረዋል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

## 4.2 ቱርክ

ቱሩክ በአሁን ሰዓት በቴክኖሎጂ አብዮት ውስጥ ከሚገኙ አገሮች እንዳዋ ተደርጋ የምትወሰድ ሲሆን በአሁን ሰዓት በከፍተኛ እድገት ላይ የምትገኝ አገር ነች ፡፡ ቱርክ የቴክኖሎጂ ወጤቶች ከማምረት በተጨማሪ ማንኛኛውም የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት በቴክኖሎጂ የተደገፈ እና በዘመናዊ የቴክኖሎጂ የተደገፈ ማድረግ ነው ፡፡ ከዚህ አካያ ቱርክ የመሬት አስተዳደር ስርዓት ግልፅ በሆነ አሰራር ለማዘመን፤ በቁጠባ እና ወጤታማ በሆነ መንገድ ለመጠቀም ከ100 ዓመት በላይ የተለያዩ ማሻሻያዎች ተግባራዊ አድርጋለች ፡፡ በዓለም አቀድ ደረጃ ከመሬት አጠቃጠም ግልፅነት ደረጃ ( Land Transparency Index ) አንፃር በተሻለ ደረጃ የምትጠቀስ አገር ነች ፡፡ ከመሬት አስተዳደር ጋር በተያያዘ ቱርክ ከወሰደቻቸው እርምጃዎች አንዱ ሁሉም የመንግስት አገልግሎቶች ገልፅ መሆን አለባቸው የሚል ህግ ያላት ሲሆን በዚህ መሰረት ከመሬት ጋር በተያያዘ ያሉ ሁሉም የመሬት መረጃዎች እና ግብይቶች ለመመዝገብ የሚያስችል የመሬት ምዝገባ እና አስተዳደር መረጃ ( Land Register and Cadaster Information system ) ያላት ሲሆን ከሁሉም የላይኛው እና የታችኛውም የመንግስት መዋቅር ዌብሳይቶች ጋር እንዲገናኝ ተደርገዋል፡፡ ይህም በወር ብቻ የመረጃ ቋቱ ከ66

ሚልዮን በላይ ህዝብ በወር ይጎበኘዋል፡፡ መረጃዎች በዚህ ሲስተም መሰረት ለህዝቡ ግልፅ እንዲሆኑ ለምሳሌ የተቸኛው የመንግስት መዋቅሮች የመሬት አጠቃቀም እና ልማት እቅድ ለመዋቅሩ እንድያሳውቁ የሚያሰግድድ ( Zoning law NR.3194 ) የሚል ህግ አላቸው ፡፡ በዚህ ህግ መሰረት የመሬት ዋጋ ፣ ለገበያ የሚውል የሪልስቴት ቦታዎች በየግዘው ከሚሻሻል የዋጋ ተመን ( Valuation ) እንዲኖራቸው ያስገድዳል ፡፡ ከቱርክ ዜጎች በተጨማሪ የመሬት ምዝገባ እና አሰተዳደር መረጃ ማንኛውም የውጭ አካል እንድያየው በሚያስችል መልኩ የተቀረፀ በመሆኑ ማንኛውም ሰው ስለቱርክ የመሬት አሰተዳደር እና የገበያ ሰርዓት በተሟላ ሁኔታ መረጃ እንዲኖረው በሚያስችል መልኩ ዲዛይን የተደረገ አሰራር ነው ፡፡ የተወሰኑ አካላት ካልሆነ በስተቀር ሲስተሙ ላይ ያሉ መረጃዎች ማንኛውም ሰው ያለ ምንም ክፍያ ማየት የሚችልበት ሰርዓት የተዘረጋ ነው፡፡ በሲስተሙ የተገለፁ መረጃዎች ላይ ጠለቅ ያለ መረጃ የሚፈልግ አካል ሲስተሙ ተጨማሪ ዝርዝር መረጃ ለመስጠት የሚያስችል ሰርዓት የተዘረጋለት ሲስተም ነው ፡፡

ቱርክ አጠቃላይ በመሬት አስተዳደር ላይ በዘረጋቹ የአሰተዳደር ስርዓት (Land Governance System) በdoing Business ፣ በquality of Land Administration index እንዲሁም በGlobal Realstate Transparency index ከ30 ነጥብ 23 በማምጣት ከፍተኛ ደረጃ ላይ የተቀመጠች አገር ነች፡፡ ይህ የሚያሳየው ቱርክ በወሰደቹ የመሬት አሰተዳደር አጠቃላይ ሪፎርም እና በቴክኖሎጂ የማዘመን ስራ ሙስና በብቃት ለመከላከል እና ለማጋለጥ የሚያስችል ነው፡፡

### 4.3 ቦሊቪያ

ሁሉ አቀፍ የተደራጀ የሕግ እና ተቋማዊ ማዕቀፍ(Comprehensive legal and institutional Frame works) መኖር ለተለያዩ ጉዳዮች ወሳኝ ነው ፡፡ በተለይም እንደ መሬት ያሉ በጣም ተጋላጭነት ባህሪ ያላቸው የስራ ዘርፎች ከሙስናና ብልሹ አሰራር በፀዳ መልኩ እንዲከናወኑ የስራ ዘርፉ ባህሪ በጥልቅ የሚዳስስ ፣ ግልፅና እና የተደራጀ የህግ ማዕቀፍ መኖር ወሳኝ ጉዳይ ነው ፡፡ ግልፅ የሆነ የህግ እና ተቋማዊ ማዕቀፍ አለመኖር በአንድ አገልግሎት የተቋማት የኃላፊነት ግልፅ አለመሆን፣ የኃላፊነት መደራረብ፣ እና በፌደራል እና በማዕከላዊ መንግስት መሀከል የግጭት መንስኤ ሊሆን ይችላል፡፡ በመሆኑም ይህን ዓይነቱን ችግር ለመቅረፍ ወይም ለመቀነስ ተያያዥነት ያላቸውን የመሬት ፖሊሲዎች ሕጎች እና ተቋማት ለማገናኘት የሚረዳ ፖሊሲና ስትራቴጂ በመቅረጽ የተሰጣቸውን ተቋማዊ ተልዕኮ ለመወጣት እርስ በርሳቸው እንዲደጋፉ ማድረግ ይቻላል፡፡ ከዚህ አኳያ የቦሊቪያን ልምድ በጥሩ ሁኔታ ማንሳት ይቻላል፡፡

በቦሊቪያ እ.ኤ.አ. ከ1999 አስከ 2010 ሁሉአቀፍ የሆነ የፀረ ሙስና ፖሊሲ በማውጣት በመሬት ላይ የሚፈፀም ሙስናን ጨምሮ ሙስናን ለመታግል ጥረት አደርጋለች፡፡ ይህ ፖሊሲ ሶስት መሰረታዊ ጉዳዮችን እንዲይዝ ተደርጎ የተቀረፀ ሲሆን ጽኑ የሆነ የሙስና ወንጀል ድርጊቶችን የሚቀጣ፣ የኢኮኖሚ

መልሶ ማጋግም በማምጣት የሕዝብን ተአማኒነት ማግኘት፣ እነዚህ ሶስት የፖሊሲው ጉዳዮች የሕግና ተቋማዊ ሪፎርም በከተማው አስተዳደር ግልፅነትን በማምጣት በተለያዩ መንገዶች የሙስና ድርጊቶችን ለማጋለጥ ወሳኝ ጉዳዮች እንደሆኑና የሀገሪቱ የቢሮክራሲ መዋቅር እንዲሻሻል በማድረግ ረገድ የራሱ የሆነ ሚና እንደተጫወተ ማየት ይቻላል፡፡

## 4.4 ታይላንድ

የመሬት አስተዳደር የማሻሻል እና ማዘመን ጉዳይ ትልቅ ትኩረት ሊሰጥበት የሚችል ጉዳይ ነው ፡፡ በመሬት አሰተዳደር ስርዓት ሶስት ነገሮችን ሊይዝ እንደሚችል ማየት የሚቻል ሲሆን ይህም ማዕካዊነት፣ ያልተማከለ የማሻሻያ ስርዓት እና መሬትን ወደ ግል የማዞር ሲሆን በማእከላዊነት የሚታይ የመሬት አስተዳደር ስርዓት የአገልግሎቱ ዓይነት አንድ ዓይነት እና የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች በመላ ሀገሪቱ የሚገኙና ሰፊ ሽፋንን የያዙ ሆነው ሲገኙ፤ ያልተማከለ የመሬት አስተዳደር ስርዓት ደግሞ የአካባቢ ፍላጎቶች በመላ ሀገሪቱ ካሉ የሚተገበር ሲሆን ሶስተኛው አማራጭ ደግሞ የመሬት አገልግሎትን የግል ማድረግ ሲሆን ይህም የመሬት አገልግሎት ውስብስበና ውጤታማ ሁኔታዎች ቢሮክራሲውን አገልግሎት ውጤታማነት ለማሻሻል እና ተአማኒም ለማድረግ ተግባር ላይ የሚውል ሲሆን ለግል ካምፓኒዎች ውል በሚከፋፈልበት ወቅት ፈተና የሚሆነው የሀገርን ጥቅም ከማስቀደም ይልቅ የግል ጥቅም ጎልቶ ሊታይ እንደሚችል ስጋት ያለበት ጉዳይ ነው፡፡

የታይላንድ መንግስት የመሬት አስተዳደር የምዝገባ ስርዓትን ውጤታማ ለማድረግ የቀን የመሬት የበላቤትነት ወይም ዝውውር ምዝገባ ስርዓትን ስታንዳርድ በማውጣት ተግባራዊ ያደረገ ሲሆን የመሬት አስተዳደር ሠራተኞች ወደ ቤታቸው የሚሄዱት በቀን ሊሰሩ በስታንዳርድ የተሰጣቸውን የመሬት ጉዳዮች ስራ ሳያጠናቅቁ እንደማይሄዱ የስራ መመሪያ ይሰጣቸዋል፡፡ በዚህም የስራ መጨናነቅ እንዳይኖር እያንዳንዱ የመሬት ቢሮ በሚያስተናግደው የፋይሎች መጠን ተሰልቶ 100,000 ፋይሎችን እንዲያይ የተወሰነ ነው፡፡ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሰነዱ ከዚህ የበለጠ አዲስ ቢሮ እንዲደራጅ ይደረጋል፡፡ ይህ የሚያሳየው ስራውን በተገቢ ሁኔታ ለመምራት የሚያስችል ዘመናዊ አሰራር እና አደረጃጀት በመፍጠር አሰራሩን ቀልጣፋ እና ፈጣን እንዲሆን ለማድረግ ያግዛል፡፡

## 4.5 አልባኒያ

የመሬት ሙስናን ለመቅረፍ ግልፅነት ያለው አሰራር ወሳኝ ነው፡፡ ይህም ተቋማት አሰራራቸውን ግልፅ በማድረግ ተጠያቂ እንዲሆኑ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህም የመሬት ፖሊሲ በሚወጣበት ወቅት ግልፅ የሆነ ግብ፣የተቋማት ኃላፊነት ምን እንደሆነ እና ለውጤታማ ግልፅ የሆነ የመሬት አስተዳደር ስራ አፈፃፀም እንዲሁም በየጊዜው ስለሚወሰዱ እርምጃዎች ጭምር በግልፅ ሊያስቀምጥ ይገባል፡፡

አልባኒያ ግልፅነትን የሚፈጥር የመሬት አሰራር በማሳደግ የመንግስት መሬት ወደ አካባቢ የአስተዳደር አካላት የሚተላለፍበትን ስርዓት ዘርግታለች፡፡ በዚህ መሰረት የአካባቢ አስተዳደር አካላት የሚተላፉ የመሬት የመንግስት መሬት ዝርዝር ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ሊተላለፉ እንደሚችሉና እንዳማይችሉ ያቀርባል፡፡ የሚኒስትሮች ምክር ቤትም የመጀመሪያ ውሳኔውን በሚተላለፉ የመሬት ዝርዝሮች ላይ ያስተላልፋል፡፡የአካባቢ አስተዳደሮችም በተሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር ከተሰኙ ይግባኝ ማቅረብ እንደሚችሉና ከዚያ በኂላ ግን ምክር ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔውን እንደሚያስተላልፍ የሚያመላክቱ ስርዓቶችን አስቀምጣለች፡፡

## 4.6. ህንድ

በመሬት አስተዳደር ላይ ተጠያቂነት ያለው አሰራር መኖሩ የሚሰጠውን አገልግሎት ከማሻሻሉም ባሻገር የመንግስት ተግባራት ምሉነትን የሚያረጋግጥ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ አንዱ መንገድ ከሆነው ውስጥ ጠንካራ እና ውጤታማ የሆነ የተቋማት የቁጥጥር ስርዓት ሲሆን ይህም የፓርላማ ቋሚ ኮሚቴ በመሰየም፣ የፀረ ሙስና ተቋማት፣ የሕግ አስከባሪ አካላት ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ ጠንካራ የሆነ ተቋማዊ የሆነ የተጠያቂነት እርምጃዎች ለምሳሌ የፋይናንስ ተቋጣጣሪዎች፣ነፃና ገለልተኛ የሆነ የመሬት ቀያሾችን ስራ ኦዲት የሚያደርግ፣ የካሳ ክፍያ ዕቅድ ትክክለኝነት የሚያጣራ ነፃና ገለልተኛ የሆነ የሕዝብ ገምጋሚ ኮሚቴ መኖር የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ተጠያቂነትን ከማረጋገጥ አኳያ ሕንድ የማህተመ ጋንዲ የፀረ ድህነት ፖሊሲ The anti-poverty policy Mahatma Gandhi National Rural Employment Guarantee Act (MGNREGA) ጠንካራ የሆነ የግልፅነት አሰራሮችን የሚያስቀምጥ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ አስገዳጅ የሆነ ማህበረሰባዊ ኦዲትን ይዟል፡፡ የቁጥጥር እና ኦዲቲን አፈፃፀም ሒደት በግልፅ የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው ውጤታማ የሕግ እርምጃዎች ውስጥ እንደ መረጃ የማግኘት መብት ሕግ የግልፅነትና ተጠያቂነት እርምጃዎችን የሚደነግግ ሲሆን የመሬት መረጃን በኦንላይን በትክክለኛ ጊዜ የመልቀቅ ግዴታን የሚያስቀምጥ ሲሆን በዚህ መረጃ ላይ ተመስርቶ የማሕበረሰብ ኦዲት በመደበኛነት ይከናወናል፡፡ ይህም ነፃና ገለልተኛ በሆነ ማሕበረሰባዊ የማሕበረሰብ ኦዲት ተጠያቂናትና ግልፅነት (Society for Social Audit Accountability and Transparency (SSAAT) የሚለው ተቋም ይህንን ስራ በዋናነት የሚያከናውን እንደሆነ ጥናቶች ያስረዳሉ፡፡

### በደቡባዊ ህንድ የካራንታካ ክልልላዊ መንግስት

በደቡባዊ ህንድ የካራንታካ ክልልላዊ መንግስት በመሬት ሴክተር የኢ ገቨርንመንትን ተግባራዊ በማድረግ ሙስና እንዲቀንስ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ በመሬት ዙሪያ መረጃዎችን ኮምፒየተራዝድ የማድረግ ፕሮጀክት የ10 ዓመት ጊዜ የወሰደ ሲሆን ፣ በዚህ ጊዜ ውስጥ የ6 ነጥብ 7 ሚሊዮን ገበሬዎች የመሬት

ባለቤትነት መረጃዎችን በጥራት አደራጅተዋል። ፕሮጄክቱ ሲጠናቀቅ ግልጽነትና ውጤታማነት እንዲጎለብት ምክንያት ሆኗል። መረጃዎቹ ለህዝብም ግልጽ በመሆናቸው ለሙስና የሚመች በር እንዲቆለፍ ተደርጓል። በማኑዋል መረጃዎች በሚጠናቀሩበት ጊዜ ተገልጋዮች ለምዝገባ ከ2 ዶላር እስከ 40 ዶላር እንዲከፍሉ ይጠበቅባቸው ነበር። ይሁንና ፕሮጄክቱ ከተጠናቀቀ በኋላ 177 የሚሆኑ የመሬት መረጃ ጉዳዮችን ለመመዝገብ 0.32 ዶላር ብቻ እንደሚያስፈልግ መረጃዎች አመልክተዋል። ስርአቱ ውጤታማነትነትን ከማረጋገጡ ባሻገር "first come" "first served" የሚለውን የአገልግሎት አሰጣጥ መርህ ተግባራዊ ያደረገ ስርአት ነው። ይህም ሰፊ የመወሰንን ፈቃደ ስልጣንን በመቀነስ የውስታና የዝምድና አሰራር እንዲወገድ ምክንያት ሆኗል። ከዚህ አኳያ በተደረገ ጥናት በማኑዋል ስራዎች በሚሰሩበት ጊዜ 66 በመቶ የሚሆኑ ዜጎች ለሙስና ይዳረጉ እንደነበርና የኢ-ገቨርንመንት ተግባራዊ ከሆነ በኋላ ግን ወደ 3በመቶ እንደወረደ ተመላክቷል። የዚህ ፕሮጄክት ሌላው ጥቅሙ አገልግሎት ለማግኘት ያለውን ውስብስብ ውጣ ውረድ ወይም ቢሮክራሲ መቀነስ ተችሏል። ከዚህ ባሻገር በመረጃዎች ላይ የሚፈጠሩ ስህተቶችን በጅጉ እንዲቀንስ ምክንያት ሆኗል።

## 4.7. ኢንዶኔዥያ

ዜጎችና የፖለቲካ ፓርቲዎች በመሬት አስተዳደር ስርዓት ላይ የሚኖራቸው ተሳትፎ የመሬት ፖሊሲ ለማውጣት እና ለማሻሻል ጠቀሜታው የጎላ ነው። የመሬት ሴክተር ፖሊሲ ሕጋዊነት የፖለቲካ አመራሩ እና ማሕበረሰቡ የጋራ መግባባት ላይ ሊደርሱ የሚገባ ሲሆን ይህ ካልሆነ ግን ጉዳዩ በጥቂት ቡድኖች ሊጠለፍ ይችላል። ይህም ሕዝቡ ነፃ ሆኖ ስለመሬት ጉዳይ ሊመክርና ካላስፈላጊ ተፅእኖዎች ነፃ ሲሆን በእርግጥም የሚወጣው የመሬት ፖሊሲ ሙስናን ለመታገል የሚያስችል እንደሆነ ጥናቶች ሲያመለክቱ ለዚህም የመሬት ፖሊሲን በተለያዩ ደረጃዎች የሚገኙ ዜጎችን በማሳተፍ የሕዝብ ተሳትፎን በማረጋገጥ ሕዝቡ የራሱን አስተዋፅኦ በሙስና ላይ እንዲያኖር ማድረግ አስፈላጊና ዋነኛው እንደሆነ ከጥናቶች መረዳት ይቻላል። ከዚህ ባለፈ ሕዝቡ በመሬት ዙሪያ የሚፈፀሙ ሙስናዎችን እንዲጠቆም ነፃ ስልክ፣ የኢሜይል አድራሻ ከማቋቋም ጀምሮ በሒደቱ ቅሬታ ያለው ዜጋ ቢኖር እንኳ የቅሬታ ማቅረቢያ ስርዓት በመዘርጋት የዜጎችን ተሳትፎ ማረጋገጥ እንደሚገባ መረዳት ይቻላል።

የሕዝብ ተሳትፎ ከማረጋገጥ አኳያ ኢንዶኔዥያ እ.ኤ.አ 2004 "የሱናማይ" ("tsunami") የመልሶ ማቋቋም ሂደት ስራ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ የንብረት ወሰንን የመለየት እና ይገባኛል ጥያቄዎች መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች አማካኝነት የሕዝብ መሬት ዝርዝር(C ommunity land inventory") ለሕዝቡ እንዲሰጥ በማድረግ ግልፅነትን ለማረጋገጥ፣ ሙስናን ለመከላከል እና የሕዝቡን መብት ለመጠበቅ እየተጠቀመችበት ነው። የይዞታ ማፒንግ እና የንብረት ቆጠራ የሚጠናቀቀው የሕዝቡን የስምምነት ፊርማ ሲያገኝ ብቻ ነው። ይህም ይዞታው አንዴ በሕዝቡ ከተፈረመበት በኋላ ወደ ብሔራዊ የመሬት አስተዳደር ኤጀንሲ ተልኮ በዚያም ሕጋዊ ስርዓቱን ተከትሎ የመሬት ፓርሴል፣

የካዳስተር ማፒነግ ስራ በመሬት አስተዳደር እና በሕግ ባለሙያዎች እንዲረጋገጥና ሕጋዊ የባለቤትነት ስርዓት እንዲረጋገጥ የሚደረግ ሲሆን ይህም በመሬት ዙሪያ የሚፈጠሩ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለማረጋገጥ ሁሉም የመሬት የምዝገባ ስራ ከክፍያ ነፃ ሆኖ እንዲከናወን ታደርጋለች፡፡

# ክፍል አምስት

## 5.በመሬት አስተዳደር ላይ የሚፈፀም ሙስና ለመከላከል እና ለመወጋት  የባለድርሻ አካላት ሚና

የመሬት አሰተዳደር ሰርዓት ብዙ ተወናዮች ያሉበት ዘርፍ ሲሆን ካለው ለሙስና ተጋላጭነት ባህሪ የብዙ አካላት ተሳትፎ እና ቅንጅት ይጠይቃል፡፡ ለዚህ ሰነድ ዝግጅት ዓላማ ታሳቢ ባደረገ መልኩ በመሬት አሰተዳደር የሚታዩ ዘርፉ ብዙ ሙስና ብልሹ አሰራር ለመቅረፍ  የሚከተሉት አካላት ተገቢን ሚናቸወን/ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡

### 5.1 . መንግስት

ሀገራችን ነበራዊ ሁኔታ  አጠቃላይ የመሬት አሰተዳደር ስርዓት በመንግስት እጅ ያለ ነው ፡፡ ይህን ግዙፍ ሆነ ሴክተር ከእያንዳንዱ ማህበረ ሰብ ፓሊቲካዊ ፤ ማህበራዊ ፤ ኢኮኖሚያዊ እና ሰብኣዊ ጉዳዮች ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ሲሆን ጠንካራ የመሬት አሰተዳደር ስርዓት ካልተፈጠረ አጠቃላይ የመንግስት አሰተዳደር ላይ ትልቅ አሉታዊ ተፅእኖ አለው፡፡ መንግስት የመሬት ምሪቱን ሰርዓቱ ወቅታዊ ፤ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ ፤ ግልፅ የሆነ ፓሊሲ ማፅቀፍ እና አሰራር የተዘረጋለት ፤ ይህን የሚያስፈፅሙ እና የሚቀጣጠሩ አካላት  በማደራጀት አጠቃላይ ማስተዳደር ብቻ ሳይሆን የአሰተዳደር ስርዓቱ በአግባቡ ተግባራዊ ሳይደረግ ሲቀር ተጠያቂነት ባረጋገጠ መልኩ እንዲከናወን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህን በቀጥታ የሚያስፈፅሙ የመንግስት ተቋማት መንግስት ያወጣቸውን ፓሊሲዎች ፤ህጎች እና ማስፈፀምያ አሰራሮች በአግባቡ ተረድተው ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በተለይም በእለተ እለት ስራ ላይ ትልቅ ሚና ያላቸው የገጠር እና የከተማ ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ተቋማት በዘመናዊ በቴክኖሎጂ የተደገፈ የመሬት መረጃ እና አሰራር ስርዓት ተግባራዊ በማድረግ ሓላፊነታቸውን በአግባቡ ሊወጡ ይገባል ፡፡ የመሬት አሰተዳደር በየግዜው ለማዘመን ተብሎ ተግባራዊ የሚደረጉ በቴክኖሎጂ የተደረጉ አሰራሮች በአግባቡ እንዲተገበሩ እና ውጤት እንድያመጡ በቁርጠኝነት መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለምሳሌ የመሬት ምዝገባ ስርዓት ( ካዳስተር ) ስርዓት በቴክኖሎጂ በተደገፈ መልኩ ለመመዘገብ ብዙ ግዜ ጥረት ቢደረገም ተጨባጭ ለውጥ ማምጣት ስላልተቻለ ይህን በቀጣይ በደንብ አጠናክሮ መቀጠል እና ተቋማት ለዚህ ቁርጠኛ መሆን አለባቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከፌዴራል ጀምሮ እስከ ታችኛቸው የመንግስት መዋቅሮች የሚያጥዋቸው ህጎች እና  የሚዘረግዋቸው አሰራሮች ወቅታዊ ፤ ተናባቢ እና አሳታፊ ሆነው እንዲወጡና ተጠቃሚ አካላት እንድያውቅዋቸው በማድረግ በኩል በትኩረት ሊሰርበት ይገባል ፡፡ መሬት ለማስተዳደር ተብሎ የሚወጡ ፓሊሲዎች  እና ህጎች የመሬት አሰተዳደር ስርዓት ውጤታማ ከማድረግ ባሻገር ለሙስናና ብልሹ አሰራር የማይፈጥሩ መሆናቸውንም ትኩረት ተሰጥቦት መሰራት ያለበት ጉዳይ ነው ፡፡ የመሬት አሰተዳደር ሰርዓት በአግባቡ

እና በቴክኖሎጂ የተደገፉ እንዲሆኑ ማድረግ አጠቃላይ በዘርፉ የሚከሰትን ሙስና ብልሹ አሰራር ለመከላከል ትልቅ ፋይዳ ይኖረዋል፡፡

## 5.2. የመሬት አሰተዳደር ተቋማት

የመሬት አሰተዳደር ተቋማት የሚያስተዳድሩት ሀብት ከሌሎች በተለየ መልኩ ትልቅ ትኩረት የሚሻ ከፍተኛ ሓላፊነት እና ስነ ምግባር የሚጠይቅ ስራ ነው፡፡ በመሬት ላይ የሚሰተዋሉ ብልሹ አሰራሮች ለመከላከል የመጀመሪያ ሓላፊነት ያላባቸው ተቋማት ከስራው ጋር ቀጥታ ግኑኝት ያላቸው ተቋማት ናቸው፡፡ እሰከ አሁን ባለው መረጀ ለፍትህ አካላት የቀረቡ የሙስና ወንጀል ጥቆማዎች እና የመልካም አሰተዳደር ቅሬታዎች ከሌሎች ዘርፍ ስራዎች ሲነፃፀር ከፍተኛ ቁጥር የሚይዝ ሲሆን ይህ ቁጥር የሚያሳየው በመሬት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚነሳው የጥራት እና ቅልጥፍና ችግር ብቻ ሳይሆን የስነ ምግባር እና የተሰጠህን ሓላፊነት በታማኝነት አለማገልገል አልፎም የሙስና ተግባራት መኖራቸውን ያሳያል፡፡ በዚህ መሰረት የመሬት አሰተዳደር ተቋማት በየግዜው ከሚነሳው ችግር ፤ ተለዋዋጭ ሁኔታ አንፃር የሚመጥን የአደረጃጀት እና አሰራር ሰርዓት፤ የሚቀርቡ ቅሬታዎች እና የስነ ምግባር መጓደል ጉዳዮች በገለልተኝነት እና በማእከል የሚፈቱበት አሰራር ፤ የወጡ ህጎች እና አሰራሮች ውጤታማ መሆናቸውን በየግዜው ኦዲት ማድረግ ፤ መፈተሸ እና ችግር ያለባቸውን እንዲሻሻሉ ማድረግ ፤ የመሬት አስተዳደር ስርዓት የመረጃ አያያዝ በቴክኖሎጂ የተደገፈ እና ከሰው ንኪኪ በፃዳ መልኩ የማዘመን ማድረግ ፤ በመልካም አሰተዳደር እና የስነ ምግባር ችግር የሚታዩባቸው ባለሙያዎች ያለ ምንም ምህረት ተጠያቂነት ማረጋገጥ ፤ መሬት አትራፊ የስራ ዘርፍ አለመሆኑን በተጨባጭ ለማረጋገጥ የወሰዱት ወይም ያገኙት ሀብት ተመለሽ እንዲሆን ማድረግ ፤ ከላይ እሰከ ታች የመሬት አሰተዳደር መዋቅር ላይ ያለው የሰው ሀብት ስምሪት እና አሰተዳደር ለስነ ምግባር ከፍተኛ ቦታ የሚሰጥ መሆን አለበት፡፡ በአጠቃላይ የመሬት አስተዳደር ተቋማት በስራቸው የሚነሱ የመልካም አስተዳደር እና የስነ ምግባር ችግሮች ለመፍታት እና የስነ ምግባር ግንባታ ላይ አትኩረው እንዲሰሩ ለየት እና ጠንከር ያለ አደረጃት መፍጠር ቢችሉ የችግሩ ስፋት መቀነስ አለባቸው፡፡ ከዚህ ውጪ ከህግ አውጪ ፤ ከኦዲት ተቋማት ፤ ከህግ ማስከበር ተቋማት ጋር በቅንጅት እና በመነባብ መስራት አለብን፡፡

## 5.3. ተቆጣጣሪ አካላት

የመሬት አስተዳደር ካላው የስራ ባህሪ አንፃር ለሙስናና ብልሹ አሰራር ከፍተኛ ተጋላጭ ሲሆን በዛው ልክ ከፍተኛ ክትትልና ቁጥር ይፈልጋል፡፡ የመሬት አሰተዳደር ከመረጀው አያያዝ ጀምሮ እሰከ ማስተዳደር ያለውን አጠቃላይ ሂደቱን በገለልተኝነት ኦዲት የሚያደርግ ፤ የወጡ ህጎች እና አሰራሮች ተፈፃሚነታቸውን የሚያረጋግጥ ፤ አለአግባብ ጥቅም ላይ ዋለ ወይም ላልተገባ ጉዳይ እንዳይውል በየግዜው ኦዲት እንድያደርጉ ሓላፊነት የሰጣቸው ተቋማት ስራቸው በአግባቡ መወጣት አለባቸው፡፡ መሬት ላይ ላይ ከተለያዩ አካላት ማለትም በተለይም ከህዝብ እንደራሴዎች ፤ ኦዲት ተቋማት ፤ የስነ

ምግባርና ፀረ ሙስና ተቋማት ፤ የእንባ ጠበቂ ተቋማት ፤ የሰብኣዊ መብት ኮሚሽን ወ.ዘ.ተ የምክረ ሀሳቦች እና የኦዲት ግኝቶች በአግባቡ ተግባራዊ እንዲያደረጉ ትልቅ ሚና አላቸው፡፡ በመሬት አሰተዳደር ተቋማት የሚሰጡ የአገልግሎቶች የእርካታ በመፈተሽ እና ጥናት በማካሄድ ውጤታማነታችን መገምገም ያስፈልጋል፡፡

## 5.4 ሚድያ እና ሲቪል ሶሳይቲዎች

ሚድያና ሲቪል ሶሳይቲዎች በማንኛውም የአንድ አገር ማህበራዊ ፤ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ እድገት እና እንቅስቃሴ ላይ የጎላ አሰተዋፀኦ አላቸው ፡፡ በተለይም ባላደገ አገር ላይ የሚኖሩ ዘርፉ ብዙ ችግሮችና የመልካም አሰተዳደር ጥያቄዎች እንዲፈቱ በማድረግ በኩል ጉልህ ሚና ይኖራቸዋል፡፡

ኪዘህ አኳያ ሲቪል ሶሳይቲዎች በመሬት አስተዳደር ላይ የሚነሱ ዘርፈ ብዙ ችግሮች በስነ ምግባር ግንባታ ፤ በምርመራ ጋዜጠኝነት ፤ የመሬት አሰተዳደር ተቋማት የሚወስንዋቸው ውሳኔዎች አግባብነት በጥናት በመፈተሸ፤ተገልጋይ እና ማህብረ ሰብ በማንቃት ፤የመሬት አሰተዳደር ተቋማት Open Data ሰርዓት ተግባራዊ እንድያደርጉ በመግፋት ትልቅ ተፅእኖ መፍጠር ይችላሉ፡፡

## 5.5 ህ/ሰብ

ህ/ሰብ ከመሬት ጋር ያላቸው ግኑኝት እና ቁርኝነት ከፍ ያለ ነው፡፡ ከእያንዳንዱ ማህበረሰብ ህይወት ጋር ቀጥታ ግኑኝነት እና መስተጋር አለው ፡፡ በዛው ልክ አጠቃላይ የመሬት አሰተዳደር ስርዓት ለሙስና ብልሹ አሰራር የተጋለጠ ከሆነ ዋነኛ ተጠቂ ማህበረሰብ ነው ፡፡ በማህረበሰቡ እና በጥቂት ግለሰቦች ከፍተኛ የሆነ የህብት ልዩነት በመፍጠር ላልተረጋጋ ማህበራዊ ፤ ኢኮኖሚያዊ እና ፓለቲካዊ ቁውስ የሚከት ነው ፡፡ ህዝብ በመንግስት ላይ እምነት እንዳይኖረው ተፅእኖው ከፍተኛ ነው ፡፡ በመሆኑም ህዝብ በመሬት አሰተዳደር የሚከሰቱ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ለመከላከል በየሰፈሩ ያሉትን ደላላዎች አሳልፎ በመሰጠት ፤የተሰጣቸውን ኃላፊነት እና እምነት ወደ ጎን በመተው ለግል ጥቅማቸው የሚሯሯጡ አመራሮች እና ሰራተኞን በማጋለጥ ከፍተኛ ሚና አለበት፡፡ በአሁኑ ሰዓት የሙስና ተግባራት እና ቅሬታዎች ለመቀበል የሚያስችል የዲጅታል የጥቆማ ስርዓት የተዘረጋ ሲሆን ይህን በማጣራት ተጠያቂነት እንዲረጋጥ በብሄራዊ ደረጃ እና በክልል/ ከተማ አሰተዳደር የፀረ ሙስና ኮሚቴዎች መቋቋማቸው ጥሩ እድል ይፈጥራል፡፡

***መረጃ መጻህፍት***